# ታይቶ ተሰምቶ አይታወቅ (ተስፋሁን ሞላ)

ታይቶ ተሰምቶ አይታውቅ በዓለም እንዲህ ያለ ነገር

ከመቃብር ሆኖ ሰው ሲመራ ሀገር

በአሁን ጊዜ ታየ በኢትዮጵያ ምድር።

ምን ነካህ ወገኔ አማራ ኦሮሞው

እስላም ክርስቲያኑ ሐረሬ ሲዳማው

ጉራጌ ከንባታ አፋሩ ጋንቤላው

እንዴት ትገዛለህ በሞተ በድን ሰው።

ያስጠይቅሃል በፈጠረህ አምላክ

ይቆጠርብሃል ጣዖት እንዳመለክ

በድን በሆነ ሰው በሞተ ስታመልክ።

መራብ መጠማት የሰው እጅ ማየትም

ከሀገር ተሰዶ መከራተት በዓለም

መከራ ችግሩ ከአንተ አይላቀቅህም።

እምብኝ ለእምነቴ ብለህ ካልተነሳህ

እምብኝ ለነጻነት ብለህ አሻፈረኝ ካላልህ

ሁልህም በአንድነት በአደባባይ ወጥተህ

መብቴ ይከበር ብለህ ካልተናገርህ

ሁሌ በሙገጫ እንደ እህል ሲወግጥህ

ይኖራል ወያኔ እረግጦ ሲገዛህ።

አንድነትን ንዶ በብሄር ከፋፍሎህ

ያልነበረ ታሪክ እሱ ታሪክ ሰጥቶህ፤

ወርዶአል ወደ መቃብር ፎቶውን ትቶልህ

በሱ እንድታመልክ ፈጣሪህን ትተህ።

ይህንም ሳያደርግ ጭፍራው አይለቅህም፤

ካልተባበርክበት ተሎ በአንድነት ሁልህም፤

እጅ ለእጅ ተያይዘህ በፍቅር በሰላም።

በቋንቋ በብሄር እንዲሁም በሃይማኖት

ጣልቃ ያልገባ የአመነ በአንድነት

እውነተኛ መሪ የድኅዎች አባት

ሌባና ቀጣፊን የአጠፋ መሳፍንት

አንድ ጀግና ነበር የቋራ ባለ አባት።

ምን አለ ቢመጣ እሱን የመሰለ

ድኅም በአለፈለት ቀመኛ ቀጣፊም እጁ በሰለለ

ሀገር አማን ሆኖ ሰው በሰላም በአደረ በዋለ።

የዘር ልክፍት ይዞት በቋንቋ የሚያምን

የውሸት ቆብ ጭኖ የሚያደናግር ሕዝብን

አሁን ባየህልን አስመሳዩን ካህን

ትገርፈው ነበረ አስወልቀህ ቆቡን።

ታሪክና ሃይማኖት ሁሉንም አጥፍተህ

የእግዚአብሔርን ቃል ወንጌልን አቃጥለህ

ከላይ እሳት፣ ወርዶ አመድ ዶግ ያድርግህ

ወያኔ የሚሉህ ቡድን ከትግራይ የበቀልህ።

ትግሬም አታመልጥ ከተጠያቂነት

አጥፍተሃል ኢትዮጵያን ዘምተህ በአንድነት

አስጨፍጭፈሃል ሕዝቧን ለሃያ ሁለት ዓመት

አዝለህ ያመጣህው ከትግራይ በረሃ ከዚያ ከደደቢት።

18/05/2013